# በውሳኔው ኢትዮጵያ የጠበቀችውንና የፈለገችውን ስታገኝ፣ ኤርትራ የወረረችውን

ዘሄግ የተሰየመው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ማካለል ኮሚሽን በሁለቱ ሀገሮች መካከል የተካሄደውን ክርክር ባቀረቡት ተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ሰሞኑን ባስተላለፈው ውሳኔ ኢትዮጵያ ድል መቀዳጀቷ ተበሥሯል:: በአንጻሩ የሻዕቢያ መንግሥት በጦርነቱ ያጋጠመውን ሽንፈት በድጋሚ በፍትሕ አደባባይ እንዲጋት ተደርጓል:: በውሳኔው ኢትዮጵያ የጠበቀችውንና የፈለገችውን ቦታ ሁሉ አግኝታለች:: ይህንኑ በተመለከተ ሁለት የውጭ ጉዳይ ከፍተኛ ባለሥልጣናት መግለጫ መስጠታቸው ይታወቃል::

በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ የሆኑት አምባሳደር ፍስሐ ይመርና ሚኒስትር ሰይፈሥላሴ ለማ ባለፈው ረቡዕ ከጋዜ ጠኞች ጋር ያደረጉትን ቃለምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል::

ጥያቄ:- የኢትዮ- ኤርትራን ድንበር ለመወሰን የተካሄደው ክርክር ሂደት ምን ይመስል እንደነበር ከኮሚሽኑ አመሠራ ረት ጋር ቢገልጹልን?

አምባሳደር ፍስሐ ይመር:- የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን የተቋቋመው በአልጀርሱ ስምምነት ነው:: የአልጀርስ ስምምነት እንደ አውሮጠውያን አቆጣጠር በታኅሣሥ ወር 2000 ዓ.ም ነው የተደረገው:: ስምምነቱ ሲፈረም ከያዛቸው ጉዳዮች በዋነኛነት የሚጠቀሰው የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ኮሚሽንን ማቋቋምን ነው:: በተደጋጋሚ ድንበር የሚለውን የምገልጸው ጉዳዩ የድንበር ጥያቄ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው::

ኮሚሽኑ እንዴት እንደሚቋቋም፣ መቼ ሥራ እንደሚጀምር፣ እንዴት ውሳኔ እንደ ሚሰጥ በስምምነቱ ውስጥ በሚገባ ተጠቅሶ ነበር:: ኮሚሽኑን ሁለቱ ሀገሮች ናቸው ለማ ቋቋም የተስማሙት:: እያንዳንዱ ወገን ሁለት ሁለት ዳኞችን ይመርጣል:: አራቱ ዳኞች ፕሬዚዳንቱን ይመርጣሉ:: ይህ ተከናውኗል:: ከዚህ በኋላ ኮሚሽኑ የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንብ አወጣ:: ከሁለቱ ሀገሮች ጋር ከተመካከረ በኋላ ተቀባይነት አገኘ:: ከዚያም ሁለቱ ወገኖች መከራከሪያቸውን በሰነድ የማቅረቡ ሂደት በፕሮግራሙ መሠረት ተከናወነ::

እያንዳንዱ ወገን ያለውን መከራከሪያ ሰነዱን ማስረጃውን አቀረበ:: ይህ ብዙ ጊዜ ነው የፈጀው:: በመጨረሻ ሁለቱ ወገኖች በኮ ሚሽኑ ፊት ሁለት ሳምንት የፈጀ የቃል ክርክር አደረጉ::

ከዚያም ለሦስት ወራት ያህል ኮሚሽኑ ሲመክር ቆይቶ ውሳኔው ሚያዝያ 5 ቀን 1994 ዓ.ም ተሰጠ::

ጥያቄ:- የኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረባ ቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ምን ይመስሉ ነበር? በአንፃሩ ደግሞ የኤርትራ መንግሥትስ ያቀረ ባቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ምን ዓይነት ነበሩ? የኢትዮጵያ መንግሥት ካቀረባቸው የመከራ ከሪያ ነጥቦች ተቀባይነት እንዲያገኙ የተደረገው ጥረት ምን ይመስላል?

ሚኒስትር ሰይፈሥላሴ ለማ:- የኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረበውን የመከራከ ሪያ ነጥብ ዝርዝር ለማቅረብ አስቸጋሪ ይመስ ለኛል:: በርካታ ናቸው:: በይዘትም ቴክኒካዊ ስለሚሆን በጥልቀት ገብቶ ለመግለጽ አስቸጋሪ ይሆናል:: የሆነው ሆኖ ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥባችን ያተኮረው ስምምነቱና የስምምነት ትርጓሜን መሠረት በማድረግ ነው::

በአንፃሩ የኤርትራ መንግሥት ዋነኛ መከራከሪያው ካርታ ነው:: በካርታ ላይ የተመ ሠረተ ክርክር ነው ሲያካሂድ የቆየው::

የሁለቱን ሀገሮች ድንበር የሚገልጹት ስምምነቶች የተደረጉት በአድዋ ጦርነት ማግስት ነው:: በአጼ ምኒልክና በጣልያን መንግሥት መካከል የተደረጉ ስምምነቶች ናቸው:: ስምምነቶቹ የተደረጉት በአድዋ ጦርነት ማግስት በመሆናቸው ምክንያት ጣልያኖች በስምምነቱ የሚገባንን አጥተናል የሚል ግንዛቤ ስለነበራቸው በየቀኑ በተቻለ መጠን ድንበሩን ወደታች ሲገፉት ቆይተዋል:: ድንበሩን በመ ሬት ላይ በመግፋት ሳይወሰኑ ያን ደግሞ በካርታ ለመደገፍ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: በመሆኑም በየቦታው የምንመለከታቸው ምናልባትም በሺ ባይሆን በመቶዎች የሚቆ ጠሩ ካርታዎች በሙሉ ለዓመታት ጣልያኖች ሲሠሩአቸው የቆዩ ካርታዎች ናቸው::

እነዚህ ካርታዎች ጣልያኖች በወረቀት ላይ ወረራ ያካሄዱባቸው ሠነዶች ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ ስምምነቱን የጣሱ ካርታዎችን ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ባጋጣሚ ደግሞ በኛም በኩል ማስተካከያ ሳይደረግባቸው የጣልያን ካርታዎችን እንዳለ ገልብጠን ስንጠቀምባቸው ኖረናል፡፡

እያንዳንዳችን በየቢሮአችን ያሉትን ካርታዎች ተመልሰን ብንመለከታቸው የኤር ትራን የይገባኛል ጥያቄ በቀጥታ የሚያንፀባርቁ ካርታዎች ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ የይገባኛል ጥያቄ ጋር የማይገናኙ፣ የኤርትራን የይገባኛል ጥያቄ የሚያረጋግጡ ካርታዎች ናቸው፡፡ ይህ የሚረዳቸው በመሆኑ የኤርትራ ወገን የተከ ራከረው ካርታውን መሠረት በ ማድረግ ሲሆን፣ እኛ ደግሞ ስምምነቱን መሠረት ያደረገ ክርክር ነው ያካሄድነው፡፡

ስምምነቱ በካርታ ተጥሷል፡፡ በምድር ላይም ተጥሷል፡፡ ስለዚህ አንዱ መከራከሪያችን ስምምነቱ ነው፡፡ ከስምምነቱ ባሻገር ደግሞ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያምኑ፣ በኢትዮጵያ ሥር ነው የምንተዳደረው ብለው የሚያስቡ ኢትዮጵያውያን የሚኖ ሩበት ምድር በካርታው ግን ለጣልያን የተከለለ በርካታ የኢትዮጵያ መሬት ነበር፡፡

ከብዙዎቹ ውስጥ ኢሮብን የሚመለከት ነው፡፡ የኢሮብን ወረዳ ብንመለከት እያንዳ ንዳችን በየቢሮአችን ተሰቅሎ በምናየው ካርታ ላይ ሙሉ ለሙሉ ጣልያኖች ያስተዳድሩት በነበረው ቦታ በአሁኑ የኤርትራ ምድር ሥር የሚወድቅ ነው ካርታውን የተመለከትን እንደ ሆነ፡፡ በኛ በኩል ስምምነቱን መሠረት በማ ድረግ ካርታዎቹን ለመቃወም ጥረት አድር ገናል፡፡ ከስምምነቱ በተጨማሪ የተጠቀምነው የአስተዳደር ሠነዶችን ነው፡፡ እነዚህ በካርታ ለኤርትራ ይገባሉ የተባሉ ቦታዎች በስምምነቱ ለኛ የሚገቡ ቦታዎች ናቸው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሥር ሲተዳደሩ የቆዩና ኢ ትዮጵያ ዊነታቸውን የሚያምኑ ሙሉ ለሙሉ ኢትዮ ጵያዊ የሆኑ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የሚል ክርክር ነው ያቀረብነው፡፡

በዚህ ረገድ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የአስ ተዳደር ሠነዶችን ለፍርድ ቤቱ አቅርበናል፡፡ በስምምነቱ ላይ ዝርዝር የሆኑ የመከ ራከሪያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ የስምምነት ትርጓሜን በሚመለከት አሳማኝ የሆኑ ክርክሮችን ለማቅረብ ተችሏል፡፡ ከዚያ በመለስ ደግሞ ምንም እንኳ ባመዛኙ ካርታዎቹ የሚረዱት የጣልያን መንግሥትና ኤርትራን ነው ብንልም በተለይ ስምምነቱ በተደረገበት ዘመን አካባቢ አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦርነት አሸናፊ ሆነው በወጡ ማግስት የተደረጉ ስምምነቶች ስለነበሩ በድርድሩ ወቅት የነበራቸው አቋም ጠንካራ ነበር፡፡

በመሆኑም በስምምነቱ ወቅት የነበሩት ካርታዎች ኢትዮጵያን የሚደግፉ ካርታዎች ናቸው፡፡ ጣልያኖች ካርታውን መቀየር የጀ መሩት ከ1906 ዓ.ም ገደማ በኋላ ነው፡፡ ከዚያ በፊት የነበሩት ካርታዎች እኛን የሚረዱ ስለ ነበ ሩ ከስምምነቱና ካስተዳደር ሠነዶች በተ ጨማሪ ካርታዎቹንም ለመጠቀም ሙከራ ተደርጓል፡፡

ስምምነቱ በተደረገበት ጊዜ የነበሩት ካርታዎች ለኛ ክርክር የራሳቸውን ጠንካራ አስተዋፅኦ አድርገዋል ማለት እንችላለን፡፡

ጥያቄ፡- የድንበር ክርክሩ በቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት መከናወኑ ኢትዮጵያን በደካማ አቋም ላይ እንድትገኝ ያደርጋታል የሚሉ ወገኖች ነበሩ፡፡ ይሄ ደግሞ ያኔ የተስማማናችው ከኃያላን መንግሥታት ጋር ስለነበር ውሎቹ ለኢ ትዮጵያ አይጠቅሙምና ልንመራባቸው አይገባም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እንዴት ትመለከቱታላችሁ? ከዚህ ጋር በተያያዘ አሰብን በተመለከተ መንግሥት ሕጋዊ መሠረት የለውም ብሎ ከሚተወው አቅርቦ ዕድሉን መሞከር አይቻልም ነበር ወይ?

አምባሳደር ፍስሐ ይመር፡- የድንበር ክርክሩ በቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት መከና ወኑ ኢትዮጵያን በደካማ አቋም ላይ ይጥላታል ለተባለው ይህ አባባል የቅኝ ግዛት ውሎች ሲደረጉ ኢትዮጵያን የሚጎዱ ነበሩ ብሎ መገ መት ማለት ነው፡፡ ይህ ግምት ትክክል አይደ ለም፡፡ በጊዜው ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሁሉም የቅኝ ገዥዎች ጋር ያደረጓቸው ውሎች ብዙ ናቸው፡፡

በሰሜን ከጣልያን፣ በምዕራብ ከእን ግሊዝ፣ በደቡብ ከጣልያን፣ በምሥራቅ ከፈረን ሣይና ከእንግሊዝ ጋር የተደረጉት ውሎች በሙሉ ከ1897 ዓ.ም ጀምሮ ባሉ ጊዜያቶች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ ውሎች ኢትዮጵያን በደካማ ጎኗ በጊዜው ያስቀምጡ ነበር ማለት አይቻልም፡፡

በአድዋ ማግስት የተደረጉ ውሎች ስለነበሩ ኢትዮጵያ በጠንካራ ሁኔታ ላይ ስለነበረች ውሉን የተደራደረችው በጠንካራ

አቋም ነው:: ውሎቹንም ይዘን ስንመለከታቸው ደካማነትን አያንፀባርቁም:: ውሎቹ ብዙም የተወሳሰቡ አይደሉም:: ማንም ሰው አንብቦ በቀላሉ የሚረዳቸው ናቸው:: ያንን ተመልክቶ ኢትዮጵያን በሙሉ የሚጎዱ ነበሩ ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል::

እነዚህ ውሎች አሁንም ቢሆን ከጎረቤቶቻችን ጋር ያሉትን ስምምነቶች የሚይዙ ናቸው:: ከኬንያ ጋር ያለን ስምምነት፣ ያለው ድንበር የተወሰነውና በመሬት ላይ የተለየው እንግሊዝና ኢትዮጵያ በ1947 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት ነው:: ከዚያ በ1970 ዓ.ም ኬንያ ነፃ ስትወጣ በመሬት ላይ ተከለለ:: መሠረቱ ግን የቅኝ ግዛት ውሉ ነው::

ከሱዳን ጋርም ያለው በመሬት ላይ በሚገባ አይካለል እንጂ አሁን ያለው ድንበር በቅኝ ግዛት ውል መሠረት ነው:: ከጅቡቲ ጋርም ያለው ይሄው ነው:: ከፈረንሣይ ጋር ባለው ስምምነት በሚገባ የተካለለ ነው:: እነዚህ ስምምነቶች አይጠቅሙንምና ልንመራባቸው አይገባም ማለት በነዚህ መሠረት የተደረጉ ድንበሮች ዋጋ የላቸውም ማለት ነው ከሕግ አንፃር:: ይህ ከሆነ ድንበራችን በምንድነው የሚገዛው? በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

ድንበሮች በዓለም ላይ በውል ነው የተመሠረቱት፣ በመሬት ላይም የሚካለሉት:: ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የውጭ ቅኝ ገዥዎችን ተቋቁመው የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ ውሎች ነው ያደረጉት:: የስምምነቶቹ ድርድር ከባድና አስቸጋሪዎች ነበሩ:: ነገርግን ታሪኩ የሚያስረዳው የውጭ ቅኝ ገዢዎች የፈለጉትን እንዲያገኙ ጥረት ቢያደርጉም ዳግማዊ አጼ ምኒልክ እንዳልተንበረከኩላቸው ነው::

ድንበሮች በየጊዜው አይለዋወጡም:: ድንበሮች የሚቀጥሉ ናቸው:: መሠረቱ ደግሞ ውል ነው:: አንዱን ብቻ ነጥሎ ዋጋ የለውም ማለት ሌሎቹስ ምን ይሆናሉ? የዚህ አነጋገር ውጤት ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል:: መልሱ ግልጽ ነው::

ከሱዳን፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ ኬንያ ጋር ያለው ድንበር አንድ ዓይነት ነው:: ጊዜው እንኳ ተመሳሳይ ነው:: ከ1897 ቢበዛ እስከ 1907 ዓ.ም ድረስ የተደረጉ ስምምነቶች ናቸው:: ወደኋላ ተመልሶ አንዱን ስምምነት ዋጋ የለውም ካልን ሁሉንም ዋጋ የለውም ማለት አለብን ማለት ነው:: ካላልን እንዴት ነው የሚሆነው? የሚስማማንን ዋጋ አለው፣ የማይስማማንን ዋጋ የለውም ማለት አይቻልም:: በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት የለውም:: መንግሥታት ሲለዋወጡ ቢውሉም የድንበር ውሎች አይለዋወጡም፣ አይነኩም የሚል መሠረታዊ መርህም አለ::

አሰብን በተመለከተ በጣም ብዙ ተተች ቶበታል፣ ብዙ መልስ ተሰጥቶበታል:: በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ብዙ ማብራሪያ ሰጥተውበታል:: የአሰብ ጥያቄን በድርድሩ ለምን ለማቅረብ አልተሞከረም የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ መልሱ አይቻልም ነበር ነው:: የአልጀርሱ ስምምነት የድንበር ኮሚሽን ሲያቋቁም ሁለቱ ሀገሮች የሰጡት ኃላፊነት ድንበራችን ላይ ጠብ ስላለ መስመራችንን ለይልን ነው መለያው መስመር ያለበትን ቦታ አሳየን፣ እኛ ልናደርገው አልቻልንም፣ ገላግለን ነው ያሉት::

ከዚህ ውጪ ሌላ ጉዳይ አስገብቼ ልጠይቅ ሲባል የተሰጠኝ ሥልጣን ድንበራቸውን እንድንለየው እንጂ እያንዳንዳቸው በሌላው ላይ ያላቸውን ጥያቄ ለማስተናገድ አይደለም:: ስለዚህ ያቀረባችሁት ትክክል አይደለም ይላል:: ትዝብት ላይም ይጥላል:: ምክንያቱም የኮሚሽኑ ሥልጣንና ኃላፊነት በግልጽ ተቀምጧልና::

በአልጀርስ ድርድር ሲደረግ የአሰብ ጉዳይ ወይም የሌላ ጉዳይ አልተነሳም:: ምክንያቱም ጠባችን እስከ መጨረሻ ድረስ የድንበር ጉዳይ ነውና:: ያንን ድንበር ኤርትራ በኃይል ለመለወጥ ስለፈለገች ነው ጦርነት የተነሳው:: በዓለምአቀፍ ግንኙነት ድንበር በኃይል መለወጥ አይቻልም:: ክልክል ነው ብለን የመከላከል ጦርነት አድርገን ነው ያቆምነው::

ከዚያ በኋላ ድንበሩ ይለይ አልን:: በመሆኑም ስምምነቱ በዚያ ላይ ነው ያተኮረው:: ዕድልን መሞከር የሚባለው ነገር ውጤቱ የትም አያደርስም ነበር:: ከመጥፎ ግምት ጋር ባጭር የሚቀጭ ነው የሚሆነው::

ጥያቄ:- ሚያዝያ 5 ቀን 1994 ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ በዳኞቹ ላይ የተሻለ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችሉ ነበር የሚባሉ ሂደቶች አሉ:: ለምሳሌ የሕዝቦች የድጋፍ ፊርማ የማሰባሰቡና የመሳሰሉትን የኢትዮጵያ መንግሥት ለምን እነዚህንስ አልሞከራቸውም? በቅርቡ የተሰጠው ውሳኔስ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ እንዴት ነው የምታዩት?

ሚኒስትር ስይፈሥሳሲ ለማ፦ መልሱ ቀላል ይመስለኛል፡፡ ከስምምነቱም ባሻገር በብሔራዊ የሕግ የዳኝነት ሒደትም ቢ ሆን በዓለምአቀፍ የሕግ ሂደት ዳኞች የሚመሩት በሕግና በሕሊናቸው ብቻ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ነፃነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት አይ ቻልም፡፡ አምስት ዳኞች ናቸው ያሉት፡፡ ሁለቱ ዳኞች የተወከሉት በኢ ትዮጵያ ወገን፣ ሁለቱ ደግሞ በኤርትራ አራቱ ዳኞች በጋራ ተቀም  ጠው ነው ፕሬዚዳንታቸውን የመረጡት፡፡ ስለዚህ አምስቱም ዳኞች የመንግሥትም ሆነ የማ ናቸውም ዓለምአቀፍ አካል ተፅዕኖ ሳያድር ባቸው ሊወስኑ የሚችሉ ሰዎች ናቸው፡፡ በሕ ግና በሕሊናዎች ብቻ እንዳይመሩ ሊያደ ርጋቸው የሚችል ተፅዕኖ ከየትኛውም አካል ሊመጣባቸው አይችልም፡፡

በብሔራዊ ፍርድ ቤት የሚዳኝ ዳኛ ከሥራዬ እባርራለሁ ብሎ ፍርድ ያጓድላል፣ ያደላል፤ ስለዚህ በሕግና በሕሊናው ብቻ አይመ ራም ሊባል ይቻል ይሆናል፡፡ ዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት የተቀመጠን ዳኛ ግን ይሄን ለማለት አይ ቻልም፡፡

ሌላው ጉዳይ ደግሞ በዳኝነንት የተቀ መጡ ሰዎች የሕግ ሊቃውንት፣ በዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት አገልግሎት የሰጡ ዳኞች ያሉበት ነው፡፡ ስምምነቱም የሚጠይቃቸው በሕግና በሕሊ ናቸው ተመርተው እንዲወስኑ ነው፡፡

በመሆኑም ከሕጉም ሆነ ከልማዱ ውጪ በፊርማ ማሰባሰብ ተፅዕኖ ሊደርግባቸው የሚቻልበት ሁኔታም ሆነ አጋጣሚ ሊ ኖር አይቻ ልም፡፡ ስለሆነም ይህንን ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ፊርማ ማሰባሰብ እንደ አንድ ማስ ረጃ የሚያገለግል ቢሆን ኖሮ ከ100 ዓመት በፊት ኢሮብን ማን ያስተዳድር ነበር የሚለውን ማስረጃ ከጥንት የኢትዮጵያ መዛግብቶች ውስጥ እየፈለፈልን ስናወጣ በእጃችን የነበረውን የፊርማ ማሰባሰብ ጉዳይ የማናከናውንበት ምክ ንያት አልነበረም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የሀገሪቱ ግዛት እስከማንኛውም ድረስ እንዲሰፋ ይፈልጋል፡፡ እንዲያድግ ይፈልጋል፡፡ የኢ ትዮጵያ ሕጋዊ ግዛት እስከሆነና ያንን ሊያስገኝ እስከቻለ ድረስ 65 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፊርማ ዝግጁ እንደሆነ ማንም ሰው ሊረዳው የሚችለው ይመስለኛል፡፡

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ልታገኝ ይገባታል የሚባለውን በማስገኘት ረገድ በጉዳዩ ላይ ሲሳተፉ የነበሩት ሰዎች ወይም ሀገሪቱን በኃላ ፊነት የሚያስተዳድረው መንግሥት ከዚያ የበ ለጠ ፍላጎት የሚኖረው አካል ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡

ቀደም ሲል የወደብ ጥያቄ ተነስቷል፡፡ ከመንግሥት የበለጠ ወደብ ማን ይፈልጋል? ኢሮብ ላይ፣ ዛላንበሳ ላይ ከተከራ ከርን ሕጉ የሚፈቅደው በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት የምና ገኘው ነገር ከሆነ ስለ አሰብ ወደብ የማንከ ራከርበት ምን ምክንያት አለ? እያንዳንዷን ኪሎ ሜትር እያንዳንዷ ኢንች እየተቆጠረች የኢትዮጵያ መሬት የሆነችው በሙሉ ለኢት ዮጵያ እንዲመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ፊርማ ማሰባሰቡ የሚጠቅም ማስረጃ ቢሆን ኖሮ የማንጠቀምበት ጉዳይ አልነበረም፡፡

ማስረጃዎቹን በማግኘትና ክርክሩን በማጠናከር ረገድ ያልተፈነቀለ ድንጋይ፣ ያልተደረገ ጥረት የለም፡፡ ያም ቢታይ ኖሮ የማይደረግበት ምክንያት የለም፡፡

ዳኞች በሕግና በሕሊናቸው ተመርተው ውሳኔ በመስጠታቸው ኢትዮጵያ ባለድል ሆናለች፡፡

ውሳኔው ለኢትዮጵያ ያለው ጥቅም ምንድነው የሚለው እንደሚታወቀው በማን ኛውም ክርክር አሸናፊና ተሸናፊ አለ፡፡ ማንኛውም ወገን ፍርድ ቤት ሲቀርብ በተለይ የግልግል ዳኝነትን የመሰሉ አካላት ጋር ሲቀርብ አሸን ፋለሁ ብሎ ነው፡፡

የኤርትራ መንግሥት ለግልግል ዳኝነቱ የቀረበው በተሸናፊነት ነው፡፡ በዚህኛው ዙር ዳኝነት ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ አሸናፊ ሆና ወጥታለች፡፡ ይገባኛል ብላ ያቀረበችውን ግዛ ቷን ሙሉ በሙሉ አግኝታለች፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳ ነገር አለ፡፡ አንዳንድ ወገኖች ካርታዎች እያቀረቡ የኢትዮጵያ የይ ገባኛል ጥያቄ ይሄ ነበር፡፡ አሁን የተሰጠው  ይሄ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ያህል ካሬ ኪሎ ሜትር ኢትዮጵያ አጥታለች የሚል ክርክር ይነሳል፡፡

በመሠረቱ ክርክርን ስናቀርብ አጥጋቢ ያልሆነ ማስረጃ የሌለበትን በተወሰነ ደረጃ ግን በክርክር ሂደት ሊካተት የሚችል የይገባኛል ጥያቄ ይቀርባል፡፡ ጥያቄዎችን አጋንኖ ማቅረብ የተለመደ ነው፡፡ ዳኞች ሰዎች ናቸው፡፡ በፍርድ ሂደት ትልቁ ጉዳይ የሰዎቹን አዕምሮ የማሸነፍና የማሳመን ጉዳይ ነው፡፡

ይህን ደግሞ ማድረግ የሚቻለው ባንድ በኩል የይገባኛል ጥያቄን ይፋ አድርጎ ጠንካራ ማስረጃ በማቅረብ ነው:: ደከም ያለ ማስረጃ ቢኖርም የይገባኛል ጥያቄውን ሰፋ አድርጎ ማቅረብም አንዱ የአካሄድ ስልት ነው::

ይህ ሲደረግ ግን አንድ መሠረታዊ ጉዳይ አለ:: ዳኞች ሰዎች ናቸው ብያለሁ:: የፍርድ ሂደት ደግሞ በቀኑ መጨረሻ የሰውን አእምሮ የማሳመን ጥያቄ ነው:: ስለዚህ ተአማኒነት ትልቅ ጉዳይ ይሰጠዋል:: ኢትዮጵያ እያቀረበች ያለችው ጉዳይ በእውነት የሚገባትን ነው ወይ? ኢሮብን አስተዳድሬአለሁ ትላለች:: ኤርትራም አስተዳድሬአለሁ ትላለች የቱ ጋ ነው እውነት ያለው ብለው ዳኞች ከራሳቸው ሕሊና ጋር ይሟገታሉ:: የተአማኒነት ጥያቄ ትልቅ ግምት የሚሰጠው እዚ ህ ላይ ነው::

ቀደም ሲል የአሰብ ጉዳይን በተመለከተ አቅርባችሁ ለምን አናጣም ነበር የተባለው ተአማኒነትን ስለሚጎዳ ነው:: የዕብድ ጥያቄ ነው የሚሆነው:: ምክንያቱም የ1908 ዓ.ም ስምምነት ከባህር ክልል ትይዩ 60 ኪሎሜትር ወደ ውስጥ ገብቶ ድንበሩ ይለካል ነው የሚለው:: ያንን 60 ኪሎ ሜትር ተሻግሮ አሰብ ይገባናል የሚል ጥያቄ በዓለም አቀፍ ሕግ ሊቃውንት ለሆኑ፣ በዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት ከ10 ዓመታት በላይ ላገለገሉ ሰዎች ማቅረብ ትዝብት ላይ የሚጥል ጉዳይ ይሆናል:: አሰብን የመጥላት ጥያቄ አይደለም:: በሕግ ውስጥ ሊካተት የማይቻል ስለሆነ ነው::

በውሳኔው ምን አገኛችሁ ለሚለው ሙሉ ለሙሉ አሸናፊ ሆነናል:: ካቀረብነው የይገባኛል ጥያቄ ጋር በማነፃፀር አይደለም ማየት ያለብን:: የኤርትራ መንግሥት ወረራ ያካሄደው ይገባ ኛል ብሎ ነው:: በምዕራቡ በኩል በ1902 ዓ.ም ስምምነት የሚገዛ የድንበራችን ክልል ነው:: ሻዕቢያ እስከ ሽራሮ ድረስ የኔ መሬት ነው ብሎ ወረረ:: በወረራ ማግሥት አልወረርኩም በመሬቴ ላይ ነው ያለሁት አለ::

ቀጥሎ ዛላንበሳን ያዘ:: የጉሎመኽዳ አካባቢን በሙሉ ወረረ:: የዛላንበሳን አካባቢ በሙሉ ተቆጣጠረ:: የኢሮብን ወረዳም እን ዲሁ:: ባዳን ሙሉ ለሙሉ ያዘ:: በ1908 ዓ.ም ስምምነት የሚመሠረተውን የምሥራቁን የድንበር ክልል አብላጫውን ከፍተኛ ቦታ በሙሉ ተቆጣጥሮት ነበር:: እነዚህ የተጠቀሱት ሻዕቢያ የወረራቸውን ቦታዎች በሙሉ አንዱንም አላገኘም::

ድንበሩ በመሬት ላይ በሚካለልበት ጊዜ የምንለያቸው የተወሰኑ መንደሮች ምናልባት ከኛ በኩል ሄደው ሊሆን ይችላል:: በአንፃሩ ደግሞ ሰፊ መሬት ወደኛ ገብቶ ሊሆን ይችላል:: ዝርዝሩን አሁን ልገባበት አልፈልግም:: ስለ ዚህ ሻዕ ቢያ ይገባኛል ብሎ የወረራቸውን ቦታ ዎች ሙሉ ለሙሉ አጥቷል:: እኛም በክርክ ራችን ማግኘት የፈለግነው ይሄንን ነው:: የይገባ ኛል መስመራችንን አስፍተን ያቀረብነው ሻዕ ቢያ የይገባኛል ጥያቄውን እንዲያጣ ለማድረግ ነው፣ ተሳክቶልናልም:: ስለዚህ በፍርድ ሂደቱ ድል ተገኝቷል፣ እውነቱም ይሄው ነው::

ጥያቄ:- ውሳኔው ከተነገረ በኋላ የኢት ዮጵያ መንግሥት ለሕዝብ የሰጠውን መረጃ የሚቃረኑ አዳዲስ መረጃዎች እየቀረቡ ነው:: የትኛውን ማመን አለብን በሚል ግራ የተጋቡ ሰዎችም መታየት ጀምረዋል:: ለምሳሌ ማርቲን የተባለ ጋዜጠኛ ደጋግሞ ኢትዮጵያ የባድመን አካባቢ እንዳጣች ሲናገር ይደመጣል:: አንዳንድ ሰዎችም ከዚህ በመነሳት እውነተ -ን ለመረዳት ጥያቄ ሲያቀርቡ ይታያሉ:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያላችሁ አስተያየት ምንድነው? ማርቲን የተባለው ዘጋቢ የተሳሳተ መረጃ የሚያ ቀርብ ከሆነ ከምን በመነሳት ነው ትላላችሁ?

ሚኒስትር ሰይፈሥላሴ ለማ:- ሂደቱ ውስብስብ ነው:: ይህ የፍርድ ሂደት በርካታ የሕግ ሊቃውንትን፣ የታሪክ ተመራ ማሪዎችን፣ የማኅበራዊ ጉዳይ አዋቂዎችን፣ የካርታ ባለሙ ያዎችን ከፍተኛ ዕውቀትና ርብርብ የጠየቀ ሂደት ነበር::

ይሄንን ሂደት ቀደምሲል በስም የተጠቀሱት ጋዜጠኛ ይሄ ሁሉ ሙያ ኖሮአቸው ስምምነቱን በቦታው ተገኝተው መተርጎም ካልቻሉ ያስገርማል::

ቀደም ሲል እንዳልኩት በኛ በኩል በግልጽ የሚታይ ነገር ነው ያለው:: አጋጣሚው መል ካም ሆኖ እነዛላንበሳ፣ ኢ ሮብ፣ ባዳ፣ በስም እየ ተጠሩ ለኢትዮጵያ ተሰጡ እንጂ ብዙ ጊዜ የግልግል ኮሚሽኖች ፍርድ ሲሰጡ ስም አይጠሩም:: አካባቢውን በዚህ ዲግሪ ላይ በማለት ነው መስመር የሚሰጡት::

እንዳጋጣሚ ሆኖ እንደሌለው ፍርድ እነ ዛላንበሳ፣ እነ ኢሮብ፣ እነ ባዳ ስማቸው ላይ ጠራ መስመር ብቻ ተሰምሮ ቢ ሆን ኖሮ በዛሬው ቀን ደግሞ የሚነገረን እነዚህ ቦታዎች የኤርትራ መሆናቸው ነበር:: ከዚህ ለይቼ አላየውም:: ጋዜጠ ኛው እንደ ጋዜጠኛ የመሰላቸውን የሚወ ግኑትን ወገን አቋም ማስተላለፍና ማስተጋባት ይችላሉ:: ይሄ ግን ከእውነት የ

ራቀ ነው፡፡ ቅድም ያልኩትን እደግመዋለሁ፡፡ ሻዕቢያ ይገባኛል ያለውን ቦታ በቃል አይደለም የነገረን የጦር ኃይሉን አስፍሮበት አሳይቶናል፡፡

እነዚያ ቦታዎች በስም እየተጠሩ የኢት ዮጵያ ሆነዋል፡፡ ባድመ በስም ተጠርቶ ስላል ቀረበ ብቻ ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ድል ለማን ኳሰስ በጦር ሜዳና በፍርድ አደባባይ ያጡትን ለማካካስ ሲሉ ስሟ ባልተጠራ ባድመ ላይ እየተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ ይሄንን ነው በየቦታው የምንሰማው፡፡

ለምንድነው ዛላንበሳን፣ ኢሮብን፣ ባዳን ማጣታቸው የማይነገረው? ከዓለም አቀፍ ፕሬስ  ከአንዳንድ ቦታዎች ላይ የምንመለከተው ነገር የባድመን ጉዳይ አወዛጋቢ ያደርገዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የወሰነበትን ሁኔድ ስንመለከተው በዚያ በኩል ያፀደቀው መስመር ድሮ የነበረውን በሁ ሉም ካርታ ላይ የምትመለከቱትን መስመር ነው፡፡

ሻዕቢያ እኛን በወረበበት ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚሁ አገር ለሚገኙ የውጭ ዲፕሎማቶች በሙሉ ያሰራጨው ካርታ አለ፡፡ እዚያ ካርታ ላይ ይሄንኑ ዲያጎናል መስመር አስቀምጦ ባድመ የሚገኝበትን ቦታ በግልጽ አመልክቶ ይሄንን መስመር ተሻግሮ ወርሮናል ብሎ ነው ለዓለምአቀፍ ማኅበረሰብ ያሳወቀው፡፡

በነገራችን ላይ ያንኑ ሰነድ ኤርትራ ለፍርድ ቤቱ አቅርባዋለች፡፡ ኤርትራ ባቀረበ ችው ማመልከቻ ውስጥ ይሄ ካርታ አለ፡፡ ካር ታው ላይ በግልጽ መስመሩ ተሰምሮ ባድመ ከመስመሩ በታች መሆኑን አምኖ ሻዕቢያ ራሱ ያቀረበው ሰነድ አለ፡፡

ይሄ ሁሉ እያለ ነው ኢትዮጵያ ባድመን አጥታለች እየተባለ በመነገር ላይ ያለው፡፡ ስለ ዚህ መሠረታዊ፣ ግል
ጽ የሆነውንና ኢትዮጵያ በአደባባይ ያገኘችውን ድል በጓሮ በኩል ለማንኳሰስ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡

ጥያቄ፡-  ድንበሩን በመሬት ላይ የማካ ለሉ ሥራ መቼ ነው የሚጀመረው? ኢትዮጵያስ ምን ዝግጅት አድርጋለች?

አምባሳደር ፍስሐ ይመር፡- ከው ሳኔው በኋላ የሚቀጥለው ሥራ በመሬት ላይ የመካለል ተግባር ነው፡፡ ይህ ቀላል ሥራ አይደለም፡፡ ከባድ ነው፡፡ በጣም ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡፡ በመሬት ላይ መካለሉ ለድንበር ኮሚሽኑ ከተሰጠው ሥልጣን ሁለተኛውና የመጨረሻው ነው፡፡ ያንን ሳይፈፅም ሥራዬን ጨረስኩ አይልም፡፡

ማካለሉ የሚጀመረው አስፈላጊው ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ነው፡፡ የድንበር ኮሚ ሽኑ ከሁለቱ ወገኖች ጋር በመመካከር የሚያ ከናውናቸው ሥራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ራሳቸው ጊዜ ይፈጃሉ፡፡ በዝግታና በጥንቃቄ የሚከናወን ሥራ ነው፡፡ ምክንያቱም በክርክሩ ውሳኔ ላይ ለማካለሉ ጊዜ የተተው ጉዳዮች አሉ፡፡

ጥያቄ፡-  ከጣልያን ጋር የነበረውን ስምም ነት ጣልያን ራሷ አፍርሳ ኢትዮጵያን ወርራ ለች፡፡ ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ተዋህዳለች፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሀገርም ነበረች፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ስምምነቱ ሊሠራ ይችላል?

አምባሳደር ፍስሐ ይመር፡- በተደጋ ጋሚ የሚሰማው አንድ ሀገር ሌላውን ሀገር ሲወር ያደረጉት ውል ይፈርሳል ነው፡፡ እንደዚህ የሚል ዓለም አቀፍ ሕግ አላውቅም፡፡ ጦርነቱ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለን ውል ያጠፋል የሚል የዓለም አቀፍ ሕግ አላውቅም፡፡ ጣልያን ኢትዮጵያን ሲወር የተደረጉት ስምምነቶች በሙሉ ፈርሰዋል የሚል የዓለም አቀፍ ሕግ ምሑር መኖሩን እጠራጠራለሁ፡፡

ውሉ ፈርሷል ዋጋ የለውም ስንል ድንበ ሮቹ በምንድነው የሚወሰኑት የሚለውን አግባብ አይመልስም፡፡ ድንበር መ
ሠረት አለው፡፡ አባባሉ ብዙ መሠረታዊ የሆነ ዓለምአቀፍ የሕግ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ጥያቄ፡-  ኢትዮጵያ በፍርዱ ሂደት የጠየቀችውን ከመስመሩ ጀምሮ አግኝታለች ነው የምትሉት? ኤርትራ ከዚያ ያገኘችው የለም ወይ? ይህን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ሚኒስትር ሰይፈሥላሴ ለማ፡- በምዕራቡ አካባቢ ኢትዮጵያ የጠየቀችውን አግኝታለች የምትሉት ምን ያህል ትክክል ነው? የሚለውን ለመመለስ ይሄ ነገር ቀደም ብዬ ወደአነሳሁት ነጥብ ይወስደናል፡፡ የይገባኛል ጥያቄ ሲቀርብ የሚፈልገው ብቻ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የሚገባትን አይደለም በይገባኛል ጥያቄ ውስጥ የምታካትተው፡፡ አንድ ምሳሌ አስታወሰኝ፡፡ ሰውየው ከጎደኛው መኪና ይዋስና ያንን መኪና አጋጭቶ ይመልስለታል፡፡ መኪና ዬን ወስዶ አጋጭቶ

መለሰልኝ ሲል ጓደኛው ይከሰዋል። ሰውየው መኪናውን አልወሰድኩም ብሎ ይከራከራል።

መኪናውን መውሰዱ በማስረጃ ሲረጋገ ጥበት እንግዲያው የመለስኩለት መኪና የተ ገጬ አይደለም ጤነኛ ነው ይላል። ይህ የተ ፈቀደ ክርክር ነው። በሀገራችን ያሉ አንድ ዳኛ ይህ ክርክር ሲቀርብላቸው አምኖ መካድ አይቻልም ብለው ሰውየው ላይ ፈርደውበታል።

እዚህ ላይም የይገባኛል ጥያቄ ሲቀርብ ሁልጊዜ በስፋት ነው። እኛ ያቀረብነው ጥያቄ በስምምነቱ የማይገቡት የጠ የቅናቸው ቦታዎች አሉን። በነገራችን ላይ መንግሥት የሚወቀስ በት ጉዳይ በፍርድ ሂደቱ ላይ በቂ ማስረጃ ሳይሰጥ ጉዳዩን በምስጢር ይዞት መቆየቱ ነው። ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ትርፍ መሬት ጠይ ቀናል ብለን ልንናገር አንችልም። ፍርድ ከመ ሰጠቱ በፊት ቢሮ የሰቀልኩት ካርታ የኤርትራን የይገባኛል ጥያቄ የሚያንፀባርቅ ነው። ኢትዮ ጵያን የሚደግፍ አይደለም ብዬ ልናገር አልች ልም። ዛሬ ግን መናገር እችላለሁ። ፍርድ የተ ሰጠን በመሆኑ።

ስለዚህ ያቀረብነው ጥያቄ በቃላት መካከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው። ይገባናል የምንለው ጥያቄ በይገባኛል ጥያቄ ውስጥ ተካት ቷል እንጂ የይገባኛል ጥያቄአችን ትርፍ መሬ ትንም አካትቷል። በዚህ ሕግ ሂደት ማስረጃ ነው የሚመዘነው። የበለጠ ማስረጃ ያቀረበው ወገን ፍርዱን ያገኛል።

ማስረጃችን በጣም የሳሳ መሆኑን እያወ ቅን ስምምነቱ ያን እንደማይል እያወቅን የሙና ወንዝ ብሎ ሲከራከረን በስምምነት ካርታው፣ ካርታው ተሳስቷል እንደሌን ወንዝ ነው ሙና ያለው ብለን ተከራክረናል። ኮሚሽኑ ያንኑ አፅ ድቆልናል። የሙና ወንዝ ተብሎ የተወሰነው ከአሊቴና በታች ነው። አሻግሮ የእንደሌን ወንዝ እንዲወሰን ተደርጓል። በምዕራቡ በኩል ለአንዲት ቀን አስተዳደርን የማናውቀውን ቦታ ጠይቀናል። ስለዚህ የይገባኛል ጥያቄ  አቀ ራረብና መጨረሻ  የሚገኘው ውጤት ይለያ ያል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ የጠበቀችውንና የፈለገችውን አግኝታለች ወይ? በሚል ቋንቋ ብናስቀምጠው የጠበቀችውን፣ የፈለገችውን ብቻ ሳይሆን ትርፍም አግኝታለች። ልናገኝ እንችላለን ብለን የምንጠብቃቸውን ቦታዎች ሁሉ አግኝተናል። ይሄ ማለት ግን እዚህና እዚያ ትንንሽ መንደሮች በማካለሉ ሂደት ሲሄዱ አይችሉም ለማለት አይደለም። ትርፍ መሬት ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ የገባበት ሁኔታ ነው ያለው።

በጦርነቱ አሸናፊ ስለነበርን ወደ ዳኝነቱ ለመሄድ ስንወስን ባመዛኙ የኢትዮጵያን ፍላጎትና ጥያቄ እንደሚደግፈው ከፍተኛ ግንዛቤ ስለነበረ ነው። መንግሥት የቤት ሥራውን ካገባደደ በኋላ ነው ወደ ስምምነቱ የገባው፡ በፍርድ ሒደቱ እነዚህ ሂደቶች የሚ  ታጡ ቢሆኑ ኑሮ አሸናፊ ስለነበር ወደፍርድ ሂደቱ አንገባም ብለን ወደ ሌላ አማራጭ መሄድ እንችል ነበር።

addisforum2002@telecom.net.et

Let's Break The Silence

SHERATON ADDIS

© 1998 - 2002 Walta Information Center